## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ

ነሃሴ 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

የቃላትና ፅንሰ ሃሳቦች ፍቺ .......... iv
መግቢያ .......... 1
ክፍል አንድ .......... 2
የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ አስፈላጊነት፣ መሰረታዊ እሳቤዎች ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦች፣ መርሆዎች፣ የፖሊሲው ወሰን፣ ዓላማዎች፣ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን ሚና እና የመገናኛ ብዙሃን ሁኔታ .......... 2
1.1 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ አስፈላጊነት .......... 2
1.2 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ መሰረታዊ እሳቤዎች .......... 3
1.3 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ራዕይ .......... 4
1.4 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ተልዕኮ .......... 5
1.5 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ዋና ዋና ግቦች .......... 5
1.6 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ መርሆዎች .......... 5
1.7 የፖሊሲው ወሰን .......... 6
1.8 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ዓላማዎች .......... 6
1.9 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች .......... 7
1.10 የመገናኛ ብዙሃን ዋና ዋና ሚናዎች .......... 7
1.11. አጠቃላይ የመገናኛ ብዙሃን ሁኔታ .......... 8
ክፍል ሁለት .......... 9
የመገናኛ ብዙሃን የጋራ ፖሊሲዎች እና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች .......... 9
2.1 ምቹ የሕግ ማዕቀፍ መዘርጋት .......... 9
2.2 መረጃ የማግኘት መብት .......... 9
2.3 የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት .......... 10
2.4 የብሮድካስት ፈቃድ የሚሰጣቸውና የሚከለከሉ አካላት .......... 11
2.5 የመገናኛ ብዙሃን መሰረተ ልማት .......... 13
2.6 የመገናኛ ብዙሃን አመራር .......... 14
2.7 የመገናኛ ብዙሃን የይዘት ብዝሃነት እና ስብጥር .......... 15
2.8 የመገናኛ ብዙሃን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን (Universal Access) ስለማረጋገጥ .......... 16

2.9 የይዘት ምርትና ይዘትን በትብብር ስለማዘጋጀት ..... 17
2.10 ለአገራዊ ፕሮግራም ወይም ይዘት ትኩረት ስለመስጠት ..... 18
2.11 የመገናኛ ብዙሃን የሕዝብ አገልጋይነት ሚና እና ልዩ ፕሮግራም ..... 19
2.12 ይዘትና የማስታወቂያ ተፅእኖ ..... 19
2.13 የሕዝብና የንግድ መገናኛ ብዙሃን ፍትሃዊ ውድድር ..... 21
2.14 ማህበራዊ ሚዲያ ..... 22
2.15 የህትመት መገናኛ ብዙሃን የወደፊት ዕድሎች ..... 23
2.16 የመገናኛ ብዙሃን ድጋፍና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ..... 23
2.17 የመገናኛ ብዙሃን ራስን በራስ ስለመምራት እና የጋዜጠኞች ማህበራት ..... 25
2.18 የጋዜጠኞች ደህንነትና ጥበቃ ..... 26
2.19 የጋዜጠኝነት የሙያ ስነምግባር እና የብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድ ..... 26
2.20 የዜና አገልግሎት ..... 27
2.21 የአቅም ግንባታ ስራዎች ..... 27
2.22 የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል ..... 28
ክፍል ሦስት ..... 28
የመገናኛ ብዙሃን የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 28
3.1. የሕትመት መገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 29
3.1.1. በመንግስት የሚተዳደሩ ጋዜጦችና መፅሄቶች ..... 29
3.1.2. የንግድ ጋዜጦችና መፅሄቶች ..... 29
3.1.3 የማህበረሰብ ጋዜጦችና መፅሄቶች ..... 30
3.2 የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 30
3.2.1 የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ..... 31
3.2.2 የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ..... 33
3.2.3 የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ..... 33
3.3 የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ..... 35
ክፍል አራት ..... 36
ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ..... 36

**የቃላትና ፅንሰ ሃሳቦች ፍቺ**

1. **"መገናኛ ብዙሃን"** ማለት በየጊዜው የሚወጣ ኅትመትን፣ የብሮድካስት አገልግሎትን እና የበይነ መረብ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የዜና ወይም የፕሮግራም ወይም የዜና እና የፕሮግራም አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ የተቋቋሙ አካላት ሲሆኑ የዜና አገልግሎት ድርጅቶችን እና በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጭ የመገናኛ ብዙሃንን ያጠቃልላል፤
2. **"በየጊዜው የሚወጣ ህትመት"** ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም፤ ለጠቅላላው ህብረተሰብ ወይም ለአንድ የተወሰነ የሕዝብ ክፍል እንዲደርስ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መፅሄቶችን የሚያካትት የህትመት መገናኛ ብዙሃን ነው፡፡
3. **"የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት በምድር ለምድር አስተላላፊ፣ በሬዲዮ ሞገድ፣ በኬብል፣ በሳተላይት፣ ወይም እነዚህን በማቀናጀት ሥራ ላይ በሚውሉ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ወይም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሰራጫዎች አማካይነት አጠቃላይ ሕዝብን ወይም የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍልን ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በድምጽና በምስል በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ ወይም የሚሰራጭ የሕዝብ፣ የንግድና የማኅበረሰብ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ፕሮግራም ሥርጭት አገልግሎት ነው፤
4. **"የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት በአገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ በሕግ የተቋቋመ ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤት የሆነ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በመንግሥት በጀት የሚተዳደር፤ ከመንግሥት ነፃና ገለልተኛ ሆኖ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጡ ይዘቶች በማዘጋጀት ለሕዝብ የማቅረብ ግዴታ ያለበት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡
5. **"የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት ትርፍ ለማግኘት በተቋቋመ የግል ድርጅት ወይም ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ የግል ድርጅት አባል በሆነ ሌላ አካል በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚተላለፍ ወይም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

6. **“የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት”** ማለት ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ባለቤትነቱና አስተዳደሩ አገልግሎቱ ታላሚ ባደረገው ማኅበረሰብ ተወካዮችና ፍላጐት የሚመራ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ጣቢያ ለተለየ ማኅበረሰብ የሚያቀርበው የብሮድካስት አገልግሎት ሲሆን የማኅበረሰቡን አባላት ወይም ከማኅበረሰቡ ጋር ግንኙነት ያላቸው እና የማኅበረሰቡን ጥቅም ለማሳደግ የሚሰሩ ግለሰቦች በፕሮግራም መረጣና አቅርቦት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያበረታታና አገልግሎቱን በአጠቃላይ ለሕዝቡ በነፃ የሚያቀርብ ነው፡፡
7. **“የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን”** ማለት በመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት አቅራቢው ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ሥር ዋነኛ ሥራው ዜናና ፕሮግራም መሰብሰብ፣ ማዘጋጀት፣ ማጠናቀርና ማሰራጨት በሆነ ድርጅት በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ምስል፣ ድምፅ፣ ቪድዮ እና የድረ-ገፅ ፅሁፍን በመጠቀም ወይም እነዚህን በማቀናጀት መረጃ የማስተላለፍ አገልግሎት ሲሆን የማህበራዊ ሚዲያንም ያካትታል፡፡

## መግቢያ

መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ፣ በማሳወቅ፣ በማስተማርና በማዝናናት እንዲሁም የዜጎችን ሀሳብን የመግለጽ ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ በማድረግ እና የተለያዩ አመለካከቶችንና አስተያየቶችን በማስተናገድ ለዲሞክራሲ ስርዓት መዳበር ተፈላጊ የሆነው ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠርና እንዲጎለብት የሚያደርግ መሳሪያ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ ነፃነት የተረጋገጠ ከመሆኑ በተጨማሪ ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነት ኖሮት የተለያዩ አስተያየቶችን የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ተደርጎለታል፡፡ ይሁንና በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚመራበት ራሱን የቻለ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ባለመኖሩ ዘርፉን በብቃት እና በጥራት በማስፋፋት ሁሉንም የኢትዮጵያ ዜጎች የመረጃ ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም፡፡

ይህን የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ በማዘጋጀት ሂደትም የዘርፉን ዋና ዋና ችግሮች እና መከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ ጉዳዮች ለይቶ ለማወቅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥናት ተደርጓል፣ ነባራዊ ሁኔታውም ተገምግሟል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረትም የመገናኛ ብዙሃን የሚመሩበት ምቹ የሕግ ማእቀፍ አለመኖሩ፣ የመረጃ እጦት ወይም እጥረት ያለባቸው መሆኑ፣ መገናኛ ብዙሃን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት የሌላቸውና ብዝሃነትን እና ጥራትን ጠብቀው የተስፋፉ አለመሆናቸው፣ በስራ ላይ ያሉት ሕጎች የጋዜጠኞችን የስራ ነጻነት የሚጋፉ መሆናቸው የሚሉት ከተለዩ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

በመሆኑም በጥናቱ የተለዩትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ይቻል ዘንድ የሀገራችን መገናኛ ብዙሃን የሚመራበት ፖሊሲ ማዘጋጀት ወቅታዊና አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ተቀርፆ በየደረጃው በሚገኙ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባካሄደው 88ኛ መደበኛ ስብሰባ በፖሊሲው ላይ በመወያየትና ተጨማሪ ግብአቶች እንዲካተቱ በማድረግ ፖሊሲው በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

ፖሊሲው በአራት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን፣ ክፍል አንድ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ አስፈላጊነት፣ መሰረታዊ እሳቤዎች፣ ራእይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦች፣ መርሆዎች፣ የፖሊሲው ወሰን፣ አላማዎች፣ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን ዋና ዋና ሚና እና አጠቃላይ ሁኔታን አካትቶ የያዘ ነው፡፡ ክፍል ሁለት የመገናኛ ብዙሃን የጋራ ፖሊሲዎች እና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ ሦስተኛው ክፍል ለእያንዳንዱ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚያገለግሉ የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችን የያዘ ነው፡፡ ክፍል አራት ፖሊሲውን የማስፈጸም ኃላፊነት ተለይቶ የተሰጣቸውን አካላት የሚያመለክት ነው፡፡

# ክፍል አንድ

# የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ አስፈላጊነት፣ መሰረታዊ እሳቤዎች ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግቦች፣ መርሆዎች፣ የፖሊሲው ወሰን፣ ዓላማዎች፣ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን ሚና እና የመገናኛ ብዙሃን ሁኔታ

## 1.1 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ አስፈላጊነት

የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚመራበት ራሱን የቻለ ፖሊሲ ባለመኖሩ ዘርፉን በብቃትና በጥራት ለማስፋፋት፣ ነፃነቱን ለማረጋገጥና ሁሉንም ዜጎች የመረጃ ተደራሽ ለማድረግ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የፖሊሲ ሰነዱ አስፈላጊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሕገ መንግሥቱ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ፤
- ከማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር የሚጣጣምና ዘርፉ የሚመራበትን አገራዊ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ፤
- መገናኛ ብዙሃንን ለማስፋፋትና አቅማቸውን ለመገንባት የሚያስችሉ የድጋፍና ማበረታቻ ስርአቶችን ተግባራዊ ለማድረግ፣
- ፖሊሲውን መሰረት ያደረገ ምቹ የሕግ ማዕቀፍ በመዘርጋት ዘርፉን በቀጣይነት ለማሳደግ ነው።

## 1.2 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ መሰረታዊ እሳቤዎች

ሀገራችን ተቀብላ ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት እና የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ድንዳጌ አንቀጽ 19 መሰረት ማንኛውም ሰው ሃሳቡን በነጻ የመግለጽ መብት እንዳለው፣ ይህ መብትም መረጃ የመሰብሰብ፣ የማግኘትና ለሌሎች የማስተላለፍ መብትን የሚያጠቃልል ሆኖ በቃል፣ በጽሁፍ፣ በህትመት ወይም በመረጠው በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም ሃሳብን መግለፅ እንደሚቻል ተደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪም ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ያሉበት እንደ መሆኑ ለሌሎች መብቶችና ነፃነቶች፣ ለሀገር ፀጥታ፣ ለህዝብ ሰላም፣ ጤንነትና ሞራል መከበር ሲባል መብቱ በሕግ ሊገደብ እንደሚችል ተደንግጓል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 29 መሰረትም ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለፅ ነፃነት እንዳለው፤ ይህ ነፃነትም በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም በህትመት፣ በስነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም አይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፣ የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን የስነ ጥበብ

ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የፕሬስ ነፃነት የቅድመ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ስለመሆኑና የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብትን አካቶ ይዟል፡፡ ለዲሞክራሲ ስርአት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባልም ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶችን የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ተደርጎለታል፡፡ በመንግስት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ መመራት እንዳለበት በሕገ መንግስቱ ተመልክቷል፡፡ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ እንደሚችሉ፤ የጦርነት ቅስቀሳዎች እና ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ እንደሚከለከሉ በሕገ መንግስቱ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት የአመለካከት፣ ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብትን፣ የፕሬስ ነፃነትን እንዲሁም የህዝብን መረጃ የማግኘት መብት ያረጋገጠ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎንም የአመለካከትና ሃሳብን የመግለፅ መብት ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው በሚወጡ ሕጎች ሊገደብ እንደሚችል ያመላክታል፡፡

በዚህም መሰረት ይህ የፖሊሲ ሰነድ ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ እሳቤዎች ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

### 1.3 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ራዕይ

ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያከብር፣ የአመለካከትና የሃሳብ ብዝሃነትን የሚያስተናግድ፣ የዲሞክራሲ ባህልን የሚያጎለብት፣ ማህበራዊ ሃላፊነቱን የሚወጣ፣ ገለልተኛ፣ ሚዛናዊና ተወዳዳሪ መገናኛ ብዙሃን ተፈጥሮ ማየት ነው፡፡

## 1.4 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ተልዕኮ

የመገናኛ ብዙሃንን አቅም በማሳደግ፣ ተደራሽነቱን በማስፋፋት፣ መሰረተ ልማትን በማጠናከር እና የቁጥጥር ወይም ሬጉላቶሪ ስራዎችን በመስራት ተወዳዳሪነቱ የተረጋገጠ መገናኛ ብዙሃን መገንባት ይሆናል፡፡

## 1.5 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ዋና ዋና ግቦች

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

1.5.1. ሁሉም መገናኛ ብዙሃን በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን መብትና ግዴታ በመወጣት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ፤

1.5.2. አመኔታና እርካታን ማሳደግ፤

1.5.3. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት፤

1.5.4. የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም፤

1.5.5. ሀገራዊ ባህልና እሴትን ማጠናከር ናቸው፡፡

## 1.6 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ መርሆዎች

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፡-

1.6.1. ብዝሃነት፣

1.6.2. ተደራሽነት፣

1.6.3. ሙያዊ ስነ-ምግባር፣

1.6.4. ሕግን ማክበር፣

## 1.7 የፖሊሲው ወሰን

ይህ የፖሊሲ ሰነድ የሚከተሉትን የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች ያካትታል፡-

1.7.1. ጋዜጣና መጽሄት፣

1.7.2. ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን፣

1.7.3. የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን፡፡

## 1.8 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ዓላማዎች

ፖሊሲው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

1.8.1. የመገናኛ ብዙሃን ከማናቸውም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጽዕኖና ጣልቃ ገብነት መጠበቃቸውን ማረጋገጥ፤

1.8.2. የመገናኛ ብዙሃን ብዝሃነትንና ስብጥርን እንዲሁም የህብረተሰቡን መረጃ የማግኘት መብት ማረጋገጥ፤

1.8.3. የመገናኛ ብዙሃን ሙያዊ ስነ-ምግባር ተከትለው ለተገልጋዩ ሕዝብ ትክክለኛ፣ ሚዛናዊ፤ ተአማኒና ተጨባጭነት ያለው መረጃ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

1.8.4. መገናኛ ብዙሃን የዲሞክራሲያዊ ልምዶችን በማስረፅ፣ የዜጎችን ትስስር በማጠናከር፣ የአገርን አጠቃላይ ገፅታ ከፍ በማድረግ ረገድ ሊጫወቱ የሚገባቸውን ሚና ማጠናከር፣

1.8.5. የመገናኛ ብዙሃን መረጃን በማሰባሰብና በማሰራጨት ሂደት የተጠያቂነትን እሴቶችን በማዳበር የድርጅቶችን እና የግለሰቦችን መልካም ስምና ዝና እንዲሁም ሌሎች መብቶችንና ጥቅሞችን መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

## 1.9 የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች፡-

1.9.1. መገናኛ ብዙሃን በዓለም ዓቀፍ ድንጋጌዎችና በሀገሪቱ ሕገ መንግስት ላይ ተንተርሰው ለተገልጋዩ ሕዝብ አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት ሁኔታ እንዲደራጁ ማድረግ፤

1.9.2. በሕዝብና በንግድ መገናኛ ብዙሃን መካከል ፍትሃዊ ውድድር እንዲኖር ማድረግ፤

1.9.3. የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያገለግሉ የማህበረሰብ አቀፍ መገናኛ ብዙሃን የማቋቋም እድል መፍጠር፤

1.9.4. የመገናኛ ብዙሃን መሰረተ ልማትን በማስፋፋት መገናኛ ብዙሃንን በአይነት፣ በቋንቋና በቁጥር ለማስፋፋት ድጋፍ ማድረግ፤

1.9.5. የመገናኛ ብዙሃን አመራሮችና ሙያተኞች ተልዕኳቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የአቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤

## 1.10 የመገናኛ ብዙሃን ዋና ዋና ሚናዎች

1.10.1. ለሕዝቡ መረጃ መስጠት፣ ማስተማር፣ ማሳወቅና ማዝናናት፣

1.10.2. ለሰላም፣ ለልማትና ለአገራዊ ሁለንተናዊ ብልፅግና ስኬት የሕዝቡን ተሳትፎ ማሳደግ፣

1.10.3. የዜጎችን ሀሳብን የመግለጽ ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ አመለካከቶችን፣ አስተሳሰቦችንና አስተያየቶችን በማስተናገድ የዲሞክራሲ ባህልና ስርዓት ግንባታ እንዲሁም የብሄራዊ መግባባት እንዲጠናከር ማድረግ፣

1.10.4. የዜጎችን የእርስ በእርስ ግንኙነትና ትስስር ማጠናከር፣

1.10.5. የሕዝቦችን ቋንቋ፣ ባህልና ዕሴት ማስተዋወቅና ማጎልበት፣

1.10.6. የአገርን አጠቃላይ በጎ ገፅታ ከፍ ማድረግ፣

## 1.11. አጠቃላይ የመገናኛ ብዙሃን ሁኔታ

በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን በሕዝብ፣ በንግድና በማኅበረሰብ ባለቤትነት የተያዙ ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን በተገኘው መረጃ መሰረት የብሮድካስት አገልግሎትን በተመለከተ ይህ ፖሊሲ በወጣበት ጊዜ 10 የሕዝብ ሬዲዮ እና 12 የሕዝብ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች፤ 15 የንግድ ሬዲዮ እና 26 የንግድ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች፤ 54 የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲሁም 3 የትምህርት በሬዲዮ ጣቢያዎች የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የወሰዱ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል አብዛኞቹ በስርጭት ላይ ሲሆኑ የተወሰኑትም ስርጭት ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡

የሕትመት የመገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ 13 ጋዜጦች እና 10 መፅሄቶች በፌዴራልና በክልል መንግስታት ደረጃ የሚታተሙ ሲሆን፤ 13 ጋዜጦችና 12 መፅሄቶችም በግሉ ሴክተር የተያዙና በስርጭት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን፣ የግል ኦንላይን የሕትመት እና የብሮድካስት ሚዲያ ውጤቶች በስርጭት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከኢትዮጵያ የሕትመት መገናኛ ብዙሃን ቁልፍ ችግሮች መካከል ከአዲስ አበባና ከክልል ዋና ዋና ከተሞች ውጭ የሚደረገው የስርጭት ሂደት ደካማ መሆን፣ የህብረተሰቡ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እና የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም የሕትመት ዋጋ መናር እና የተጠቃሚዎች የመግዛት አቅም ማነስ ይጠቀሳሉ፡፡

# ክፍል ሁለት

# የመገናኛ ብዙሃን የጋራ ፖሊሲዎች እና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

በመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ሁሉም አይነት የመገናኛ ብዙሃን ሊከተሏቸው የሚገቡ የጋራ አሰራርና አቅጣጫዎች እንዲሁም መገናኛ ብዙሃን እንደየባህሪያቸው ሊከተሏቸው የሚገቡ የተናጠል አሰራርና አቅጣጫዎች በግልጽ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት ለሁሉም መገናኛ ብዙሃን የሚያገለግሉ የጋራ ፖሊሲዎች እና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

## 2.1 ምቹ የሕግ ማዕቀፍ መዘርጋት

በአገራችን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ለማረጋገጥ የሚወጡ ሕጎች ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው አለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶችን የማይቃረኑና የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህም መረጃ የመሰብሰብ፤ የመቀበልና የማሰራጨት እንዲሁም ምንጮችን ያለማሳወቅ መብቶች በሕግ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 29 የአመለካከትና ሃሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረኑ ሕጎች መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.2 መረጃ የማግኘት መብት

በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 29 ማንኛውም ሰው መረጃ የመሰብሰብ፤ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ዜጎች ከመንግስት ተቋማት መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ተቋማቱ መረጃ የመስጠት ግዴታቸውን እንዲወጡ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣ ሁሉም ተቋማት መረጃ በኦንላይን የሚያሰራጩበትን ዘመናዊ አሰራር ማዳበርና ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ብሔራዊ የመረጃ ማዕከል በማቋቋም መረጃ በቀላሉ የሚሰጥበት አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ እራሱን

የቻለ የመረጃ ነጻነትን የተመለከተ ሕግ ከዝርዝር ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያዎች ጋር እንዲወጣ ማድረግም ያስፈልጋል።

## 2.3 የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት

መገናኛ ብዙሃን የህዝብን የመረጃ ባለቤትነት ያረጋገጠ፣ ዋነኛ ትኩረቱም ዜጎችን የማገልገልና ዲሞክራሲ እንዲጠናከርና እንዲዳብር ለማድረግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል። በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት በሕዝብ፣ በንግድና በልዩ ልዩ ማህበረሰቦች የተያዘ ነው።

ይሁን እንጂ በአገራችን የንግድ መገናኛ ብዙሃን ባለቤትነትና ስብጥር ፍትሃዊ አይደለም። ስለሆነም በንግድ መገናኛ ብዙሃን የተለያየ ስብጥር እና ብዝሃነት ያለው የሚዲያ ምህዳር እንዲፈጠር ለማድረግ ግለሰብን ጨምሮ የንግድ ተቋማት የንግድ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ባለቤት እንዲሆኑ መፍቀድ ይገባል። ከዚህ አኳያም ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም ከፍተኛው የባለቤትነት የአክስዮን ድርሻ በኢትዮጵያውያን ይዞታና ቁጥጥር ስር እንዲውል ማድረግም ያስፈልጋል። አንድ የንግድ ድርጅት በአንድ ጊዜ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን፣ የጋዜጣና የመፅሄት ባለቤት መሆን የሚችልበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ መገናኛ ብዙሃን የሃብት ምንጫቸውን ግልፅ በማድረግ ለተደራሲያኖቻቸው ከመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች ተፅእኖ ነፃ መሆናቸውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። የንግድ መገናኛ ብዙሃን አወቃቀርን በተመለከተም የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ለማቋቋም በንግድ ማህበር መደራጀት አስፈላጊ ሲሆን፤ ጋዜጣና መፅሄት ለማሳተም ግን አንድ ግለሰብ ብቻውን በባለቤትነት እንዲያቋቁም ይደረጋል፡፡ ይህም ሲሆን በጋዜጠኛና በባለቤቱ መካከል የጥቅም ግጭቶችንና አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶችን ማስወገድ፣ በኤዲቶሪል ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ የተጠያቂነት ግንኙነት መፍጠርና ለአዘጋጅ ነጻነት የተበጀውን የሕግ ዋስትና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በብሮድካስት አገልግሎት ለመሰማራትም በመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ የማግኘት ግዴታ ሊቀመጥ ይገባል።

የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን በፌዴራል መንግስት ወይም በክልል መንግስታት ወይም በኮርፖሬሽን መልክ ሊቋቋም ይችላል፡፡ የበጀት ምንጫቸው አቅም በፈቀደ መጠን ከመደበኛው የፌዴራልና የክልል መንግስታት በጀት የተለየ ምንጭ ኖሯቸው ሊደራጁ ይገባል፡፡ ሆኖም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት የሕዝብም ሆነ የንግድ ብሮድካስት ባለቤት እንዲሆኑ ሊፈቀድ አይገባም፡፡

ለትርፍ ያልተቋቋሙ ማህበራት፣ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የጋዜጠኞችና የመገናኛ ብዙሃን ማህበራት አባላት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች አካታች በሆነ መልኩ ተደራጅተው የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ግልፅ የሆነ ዝርዝር ሕግ በማውጣት የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት ስብጥርን ማስፋት አስፈላጊ ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሃን የንብረት ቁጥጥር ሕግ አገራዊ ጥቅምን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱን፣ መገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ሰዎች መያዝን የሚያበረታታ መሆኑን፣ መገናኛ ብዙሃንን የመረጃና የሀሳብ ስብጥርንና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በማበረታታት በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻልን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 2.4 የብሮድካስት ፈቃድ የሚሰጣቸውና የሚከለከሉ አካላት

በመገናኛ ብዙሃን እና በኢንቨስትመንት ሕጎች ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የውጭ አገር ዜጎች በመገናኛ ብዙሃን ስራ መሰማራት እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ ይሁንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ፈቃድ ሳያገኙ የሚያሰራጩበት ሁኔታ በመኖሩ በዚህ ረገድ የሚያበረክቱት የካፒታልና የሙያ ሽግግር ለዘርፉ እድገት አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

ስለሆነም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ውስን ድርሻ በመያዝ በመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል የውጭ አገር ዜጋና በውጭ አገር ዜጋ የተቋቋመ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድ የሚከለከል ይሆናል፡፡ ይሁንና በውጭ አገር ተቋቁመው የሚንቀሳቀሱ መገናኛ ብዙሃን በአገር ውስጥ ቅርንጫፍ ከፍተው የሚሰሩበት ወይም የዜና ወኪል በመመደብ ከአገር ውስጥ ለማሰራጨት ፈቃድ ከጠየቁ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

የሃይማኖት ብሮድካስት ጣቢያዎችን በተመለከተም በስራ ላይ ያለው የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 የሃይማኖት ድርጅቶች የብሮድካስት ፈቃድ እንዳያገኙ ይከለክላል፡፡ ይሁንና የሃይማኖት ድርጅቶች አስተምህሮታቸውን በመገናኛ ብዙሃን ለማድረስ ይፈልጋሉ፡፡ በርካታ ህብረተሰብም ሃይማኖታዊ ፕሮግራሞችን ለመከታተል ፍላጎት አለው፡፡ ስለሆነም የሃይማኖት ተቋማት የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም ከምድር ወደ አየር ከሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት አይነት ውጪ በሌሎች ማሰራጫ መንገዶች የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይም የሃይማኖት ጣቢያዎችም ሆኑ ሌሎች ብሮድካስተሮች የሃይማኖት ፕሮግራም ለማሰራጨት ከፈለጉ የሚፈቀድላቸው ይሆናል፡፡ የሃይማኖት ጣቢያዎች የምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ እንዲሁም ተያያዥ ሁኔታዎች በመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል፣ በሃይማኖት ተቋማት እና የሃይማኖት ተቋማትን በሚመዘግበው አካል በጋራ የሚከናወን ይሆናል፡፡

በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 የብሮድካስት ፈቃድ እንዳያገኙ ከተከለከሉት ውስጥ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች የአክስዮን አባል የሆኑበት የብሮድካሰት ጣቢያ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች አመራር የሆኑበት የብሮድካሰት ጣቢያ ይገኙበታል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አመራሮች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅት ንብረቶች የብሮድካስትና የህትመት መገናኛ ብዙሃን ስራ ተሳትፎ መልስ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲ መገናኛ ብዙሃን በግልፅ የፖለቲካ ልሳን ሆነው ለመስራት ከፈለጉ በጋዜጣና መፅሄት ሕትመት እንዲስተናገዱ

የሚደረግ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጥ አይሆንም፡፡ በተጨማሪም በህዝብና በንግዱ መገናኛ ብዙሃን እና በፖለቲካ ፓርቲ ልሳኖች መካከል ያለው ልዩነትም ግልፅ መስፈርትና አሰራር የሚበጅለት ይሆናል፡፡

## 2.5 የመገናኛ ብዙሃን መሰረተ ልማት

ኢትዮጵያ በፌዴራል፣ በክልልና በአካባቢ ደረጃ የሚሰራጩ የብሮድካስት ጣቢያዎች አሏት፡፡ ይሁንና አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ዜጎች የመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ አይደሉም፡፡ በተለይም የኤሌትሪክ ኃይል የማያገኙ ዜጎች በፀሃይ ብርሃን ወይም በባትሪ ኃይል የሚሰሩ መቀበያዎችን የመግዛት አቅም ከሌላቸው የሬዲዮ ተጠቃሚ መሆን አይችሉም፡፡ የቴሌቪዥን ተደራሽነትም ቢሆን የኤሌትሪክ ኃይል ባለባቸው ከተሞችና በከተሞች አቅራቢያ በሚገኙ ቴሌቪዥን፣ ዲኮደርና ሳተላይት ዲሽ የመግዛት አቅም ባላቸው ወይም በጋራ መገልገያዎች መጠቀም በሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ የተገደበ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የበይነ-መረብ አገልግሎት እየተስፋፋ በመሆኑ ዜጎች በበይነ-መረብ አማካኝነት የመገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ የመሆን ዕድላቸው እያደገ መጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሞባይል ስልክ የሚደረግ የይዘት ስርጭት በዝቅተኛ ዋጋ ሰፊ ቦታን ለመሸፈን የሚያስችል መልካም አጋጣሚ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ለመገናኛ ብዙሃን መስፋፋት ይረዳ ዘንድ መንግስት ለመገናኛ ብዙሃን መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ የማሕበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች ከፌዴራልና ከክልል ብሮድካስተሮች ጋር ተቀናጅተው መሰረተ ልማትን በጋራ የሚጠቀሙበትን ስልት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ የብሮድካስት ማሰራጫ ኔትወርክ፣ የአንቴና ምሰሶ እና መሰል መሰረተ ልማቶችን በግልም ሆነ በጋራ በማቋቋምና ብሮድካስተሮች በቁጠባና በውጤታማነት የሚጠቀሙበት፣ በዝቅተኛ ዋጋ የሚከራዩበት እንዲሁም አማተር ባለሙያዎችን ለማበረታታት ፊልምና ፕሮግራም በነፃ የሚቀርፁበት የጋራ የሚዲያ ስቱዲዮ

ህንፃ የሚገነባበት፣ የህትመትም ሆነ የብሮድካስት ዘርፍ በየጊዜው ከቴክኖሎጂው ጋር አብሮ የሚዘምንበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 2.6 የመገናኛ ብዙሃን አመራር

የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አመራርና የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካሉን በተመለከተ የሕግና የአሰራር ክፍተቶች ይስተዋላሉ፡፡ የአብዛኛዎቹ ብሮድካስተሮች የአመራር ወይም የስልጣን ተዋረድ በማዕከል የተገደበ ነው፡፡

በመሆኑም የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን የአመራር ምደባ ሙያዊ ብቃትንና የፆታ ስብጥርን፣ ብዝሃነትንና ገለልተኛነትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን እውነተኛ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃንነቱን ለማረጋገጥ በመገናኛ ብዙሃን አመራር፣ በጋዜጠኝነት፣ በባህል፣ በኢኮኖሚና በቴክኒክ ብቃታቸው የሚታወቁ እንዲሁም በፍትሃዊነት የተወከሉ የሲቪል ማህበረሰብ አባላትን የያዘ የቦርድ አመራር ሊኖረው ይገባል፡፡ የቦርድ አባላት አስፈላጊውን የምርጫ ሂደት ያለፉና በፌዴራል ወይም በክልል የህዝብ ምክር ቤቶች ይሁንታ ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላም በኩል የፋይናንስና ኤዲቶሪያል ስልጣንና ኃላፊነትን ለታችኛው የስልጣን እርከኖች በውክልና ማውረድ አስፈላጊ ነው፡፡

የግልና የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አመራሮች በመገናኛ ብዙሃን አመራር፣ በምጣኔ ሃብት፣ በንግድ ስራ አመራር ወዘተ ያላቸውን አቅም መገንባትና ማጠናከርም ተገቢ ነው፡፡ የንግድ መገናኛ ብዙሃን የቦርድ አባላት እና ስራ አመራሮችም አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይገባል፡፡ የንግድ ብሮድካስተሮች ስራ አመራር ከየትኛውም የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ መሆን ያለበት ሲሆን፤ ከሦስተኛ ወገን የሚገኝ የኢኮኖሚ ጥቅም ካለም በሚታወቅና ግልፅ በሆነ አሠራር የሚመራ መሆን አለበት፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካሉ የቦርድ አመራሮችና ስራ አመራሮች ከላይ ለህዝብ ብሮድካስተሮች ስራ አመራር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ስብጥርና ብዝሃነትን ባማከለ ውክልና ሊዋቀር ይገባል።

## 2.7 የመገናኛ ብዙሃን የይዘት ብዝሃነት እና ስብጥር

በኢትዮጵያ ያለው የመገናኛ ብዙሃን የይዘት ብዝሃነትና ስብጥር በውስን ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። የሕዝብና የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በፍትሃዊነት ማገልገል የሚጠበቅባቸው ቢሆንም፤ ከፍተኛ የሆነ የይዘትና የቋንቋ ብዝሃነት ውስንነት ይታይባቸዋል። መደበኛው የንግድ መገናኛ ብዙሃን ተደራሽነቱ በአዲስ አበባ እና በክልል ዋና ከተሞች ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ስርጭቱ በጣም ውስን ነው። እነዚህም ቢሆኑ በኢኮኖሚ እጥረት የሚፈለገውን ያህል ጥልቅና ገንቢ የሆነ ትችት አዘል ዘገባ ለማቅረብና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ለማገልገል የሚቸገሩበት ሁኔታ ይስተዋላል።

በመሆኑም የመገናኛ ብዙሃን ስብጥርንና ብዝሃነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ጋዜጠኞች፣ ኤዲተሮች እና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ተቀዳሚ ትኩረታቸው የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሃሳብና አመለካከት ማስተናገድ ላይ ያተኮረ እንዲሆን ለጋዜጠኞች፣ ለኤዲተሮች እና ለመገናኛ ብዙሃን ተቋማት የሚሰጡ ትምህርቶችና ስልጠናዎችን ማሻሻልና ማጠናከር ያስፈልጋል። የሃሳብ ብዝሃነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሕዝብም ይሁን የንግድ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ህትመት ወይም በበይነ-መረብ አማካኝነት የሚሠራጭ መገናኛ ብዙሃን ከአጠቃላይ ይዘታቸው ቢያንስ 15 በመቶውን ቢበዛ 40 በመቶውን ለግል ይዘት አምራቾች፣ ተባባሪ አዘጋጆች ወይም የትርፍ ጊዜ ጋዜጠኞች እንዲመድቡ መደረግ ይኖርበታል።

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሄረሰቦችና ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ማህበረሰቦች የሚኖሩባት አገር ናት። በመሆኑም ሁሉም ማህበረሰቦች ከራሳቸው አካባቢና ከጎረቤት ማህበረሰቦች ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ሬዲዮ ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። በሂደትም

የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች ከአገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ አጋሮች የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

በመንግስት ገንዘብ የሚከናወኑ የመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ አመለካከቶችን በሚያስተናግዱበት ሁኔታ ሊመሩ እንደሚገባ በሕገ መንግስቱ ተቀምጧል። ስለሆነም የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለአገራዊ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በአገሪቱ የቋንቋ ፖሊሲ መነሻነት አቅም በፈቀደ መጠን ይዘቶችን በሁሉም የአገሪቱ ቋንቋዎች እንዲያሰራጩ ይደረጋል። ስለሆነም በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ተቋማት ውስጥ የጋዜጠኞች የብሔርና የፆታ ስብጥር መረጋገጥ ይኖርበታል።

## 2.8 የመገናኛ ብዙሃን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን (Universal Access) ስለማረጋገጥ

የመገናኛ ብዙሃን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት (Universal Access) ማለት የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎትን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነትና በፍትሀዊነት ማድረስ ማለት ነው። በአገራችን ለመገናኛ ብዙሃንና ለመረጃ ተደራሽ ያልሆኑ በርካታ ማህበረሰቦች ይገኛሉ።

በመሆኑም የሕዝብ፣ የንግድና የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች እንዲሁም የህትመት መገናኛ ብዙሃን የኢትዮጵያ ህዝቦችን የመረጃ ፍላጎትና ተጠቃሚነት መሰረት አድርገው መስራት አለባቸው። አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ዜጎች የመረጃ ተደራሽ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል። የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋፋት የብሮድካስት አገልግሎትን ለመላ የአገሪቱ ሕዝብ ማዳረስ ይገባል። ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ተከታታይ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሽፋን መቶ በመቶ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። የህዝብ ብሮድካስተሮች ለአካባቢ የማህበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያዎች የቴክኒክ፣ የስልጠናና የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ንብረታቸውንና የአዕምሮ ውጤታቸውን ለማህበረሰብና ለንግድ ብሮድካስተሮች በማጋራት

ተደጋግፈው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የሕዝብ ብሮድካስተሮችም የንግድ ብሮድካስተሮችን ህልውና ሳይነኩ የራሳቸውን ገቢ የሚያመነጩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ መሆን ስላለበት በበርካታ አገራት የፋይናንስ ድጋፍ (Universal Access Fund) ተመድቦለት ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ ከፍተኛ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በአገራችን ሁሉም ዜጋ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ተደራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማስፋፋትና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ዩኒቨርሳል አክሰስ ፈንድ ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የንግዱ ዘርፍም ልዩ ልዩ ሃሳቦችን በማንሸራሸር ረገድ ለዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት በመገናኛ ብዙሃን ስራ ሰፊ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይበረታታል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች የመረጃ ተደራሽ ላልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የገጠሩ ማህበረሰብ ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት በቂ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ መገናኛ ብዙሃን ለልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ለህፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሴቶችና ለአካባቢ ጉዳዮች በቂ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን ሽፋን መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ መንግስትም ለመሰል ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

## 2.9 የይዘት ምርትና ይዘትን በትብብር ስለማዘጋጀት

የይዘት ምርት አንድ ጠቃሚ የሥራ መስክና ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ከይዘት ዝግጅት ጋር በተያያዘ የአቅም ግንባታና የድጋፍ አገልግሎት በማግኘት ረገድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሌላው ዘርፍ ለብሮድካስተሮች በግብአትነት የሚያገለግለው የዜና አገልግሎት፣ የኪነጥበብ፣ ሙዚቃ፣ ድራማ፣ ቴአትር፣ የቪዲዮና ፊልም፣ የዶኩመንተሪ፣ የማስታወቂያ፣ የመዝናኛና መሰል ተዛማጅ ስራዎች ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ይህ አንዱስትሪ ይዘቶችን በአይነትና በጥራት ማምረት ከቻለ ብሮድካስተሮች ተፈላጊውን ይዘት መግዛት ስለሚችሉ ለህብረተሰቡ አይነተኛ የመረጃ ምንጭ ለመሆንና ኢንዱስትሪውንም በማሳደግ አገሪቱ ተጠቃሚ እንድትሆን ከማስቻል አኳያ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም የኢንዱስትሪው መሰረታዊ ማነቆዎች ወይም ችግሮች በጥናት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ መፈታት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም በአእምሮ ውጤቶች መብት ጥበቃ እና በሰው ሃይል፣ በፋይናንስና በቁሳቁስ ረገድ ያሉበት ችግሮች የሚቀረፉበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ የብሮድካስት ፈቃድ የጨረታ ውድድር መስፈርቶች በሚዘጋጁበት ወቅት ጣቢያዎቹ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ብዝሃነት የሚያንፀባርቁ ፍላጎቶችን ያካተቱ ይሆኑ ዘንድ ከተለያዩ የአካባቢ፣ የክልልና አገራዊ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ጋር በጋራ ይዘት የማምረት ስራ ለሚሰሩ ተቋማት ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተለያዩ የክልልና የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን መካከል የጋራ ትብብር ሲኖር በህዝቦች መካከል የጋራ መግባባት እና መተማመን ይፈጠራል፣ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የሙያ ዕድገትም የተቃና እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና የግል ይዘት አምራቾች ሙያዊ አቅም እንዲገነባ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## 2.10 ለአገራዊ ፕሮግራም ወይም ይዘት ትኩረት ስለመስጠት

ብሮድካስተሮች ጥራታቸውን የጠበቁ እና የተለያዩ ይዘት ያላቸውን አገራዊ፣ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ፕሮግራሞችን ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ስለሆነም የሕዝብ፣ የንግድና የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች ሊያቀርቡት የሚገባውን የአገራዊ ፕሮግራም ይዘት ዝቅተኛውን መጠን መወሰን እና ይህም መጠን ተግባራዊ የሚሆንበትን ጊዜ በሕግ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ለመገናኛ ብዙሃን ፈቃድ የሚሰጠው አካልም መገናኛ ብዙሃን ከሚያሰራጩት ይዘት የተወሰነ መቶኛውን ድርሻ ለአገር ውስጥ ጉዳይ እንዲመድቡ በፈቃድ ጨረታ መስፈርት ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 2.11 የመገናኛ ብዙሃን የሕዝብ አገልጋይነት ሚና እና ልዩ ፕሮግራም

የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ከማቅረብ፣ ከማሳወቅ፣ ከማስተማርና ከማዝናናት በተጨማሪ የሕዝብ ድምፅ ትኩረት አግኝቶ እንዲሰማ በማበረታታት እንዲሁም መገናኛ ብዙሃን የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ እንደመሆናቸው ውሳኔ ሰጪ የመንግስት አካላትን ግልፅኝነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ፣ በሰላም፣ በልማትና በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ወሳኝ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም መገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞችን በማሰራጨት የሕዝብ አገልጋይነት ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም መገናኛ ብዙሃን ለዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ አስፈላጊውን ሚና መጫወታቸውን፤ ብዝሃነትን በማረጋገጥ አገራዊ አንድነትን ማጠናከራቸውን፣ በመረጃ የበለፀገ ህብረተሰብ በመገንባትና መሰል የመገናኛ ብዙሃን ሚናን በመወጣት ረገድ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ማረጋገጥ ይገባል፡፡

መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ወቅታዊ መረጃ በማቅረብ፣ በማሳወቅ፣ በማስተማርና በማዝናናት እንዲሁም በምርጫ ወቅት ነፃ የአየር ሰዓት በመመደብ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ወይም ሕገ መንግስታዊ ሥርአትን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲከሰት መንግስት የሚሰጣቸውን መግለጫዎች በማሰራጨት ሃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም መገናኛ ብዙሃን በተለየ ሁኔታ ትኩረቱን በአንድ ጉዳይ ላይ ያደረገ ፕሮግራም እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡

## 2.12 ይዘትና የማስታወቂያ ተፅእኖ

የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን አብዛኛውን ጊዜ የሚተዳደሩት በሕዝብ ገንዘብ ሲሆን፤ ፕሮግራሞቹ የሚደገፉትም ዜጎች ለተለያዩ አገልግሎቶች በቀጥታ ወይም በግብር መልክ ከሚከፍሉት ክፍያና ከማስታወቂያ ገቢ ነው፡፡ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ትኩረታቸውን የአድማጭና ተመልካቾችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ወይም ለማሳደግ በሚረዱ ፕሮግራሞች

ላይ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይሁንና ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ለአድማጮች መቅረብ ያለባቸውን ፕሮግራሞች በማጠፍ ማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ በሚያስገኙ ፕሮግራሞች ላይ የሚታጠሩበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በተመሳሳይም የዲሞክራሲ ስርአት ባልተጠናከረባቸው አገራት የሚገኙ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለመንግስትና በምክር ቤት አብዛኛውን መቀመጫ ለያዘው የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኛ የሚሆኑበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡

የንግድ መገናኛ ብዙሃን ገቢያቸውን የሚያመነጩት ከማስታወቂያና ከስፖንሰርሽፕ ክፍያ ሲሆን፤ የፕሮግራም ትኩረታቸው የሚወሰነውም ፕሮግራሞቹ በሚያስገኙት አድማጭ ተመልካችና የማስታወቂያ አስነጋሪዎች ድርሻ ነው፡፡ የንግድ መገናኛ ብዙሃን ከተዳከሙ ክፍያ ለሚሰጣቸውና ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው የንግድ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተፅዕኖ እንዲጋለጡ በማድረግ የነሱን አላማ ለማስፈጸም በሚያተኩር ዘገባ ላይ እንዲጠመዱ ጫና ሊፈጥርባቸው ይችላል፡፡

በመሆኑም ሁሉም የሕዝብ፣ የንግድና የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን በፍትሃዊነት ከመንግስት የማስታወቂያ በጀት ተጠቃሚና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የመንግስት ተቋማት የማስታወቂያ በጀት ክፍፍል ግልፅ የአሰራር ስርአት ሊዘረጋለት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድም የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል በየዓመቱ የሚያከናውነው የመገናኛ ብዙሃን ተደራሲያን ድርሻ የጥናት ውጤት አንዱ የመንግስት የማስታወቂያ ገቢ ማከፋፈያ መስፈርት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

የንግድ መገናኛ ብዙሃን ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ ጎን ለጎን የመገናኛ ብዙሃንን ኤዲቶሪያል ነጻነትና የጋዜጠኝነት ሙያ የብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድ ለድርድር ሳያቀርቡ የሕዝብን የመረጃ ፍላጎት ለማርካት ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ኢኮኖሚያቸውን በቋሚነት ለማሳደግ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ መንግስትም ለንግድ መገናኛ ብዙሃኑ የፋይናንስና ሌሎች የአቅም ማሳደጊያ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በማስታወቂያ አስነጋሪዎች የሚተላለፉ የምርትና አገልግሎት የንግድ ማስታወቂያዎች የህጻናትንና የወጣቶችን ጤንነትና ደህንነት የሚነካ፣ አገራዊ ባህልና እሴትን የሚሸረሽር፣ የአልኮል መጠጦችን የሚያስተዋውቁ፣ የተዛባ የፆታ ውክልናን የያዙ መልዕክቶችን እንዲሁም ሌሎች ሕግን የሚተላለፉ መልዕእክቶችን ማሰራጨት በሕግ ሊከለከል ይገባል።

## 2.13 የሕዝብና የንግድ መገናኛ ብዙሃን ፍትሃዊ ውድድር

በማስታወቂያ አዋጁ ለሕዝብም ሆነ ለንግድ ብሮድካስተሮች የተመደበው የማስታወቂያ ጊዜ ምጣኔ ከጠቅላላ የሥርጭት ጊዜው እኩል 20 በመቶ ሲሆን፤ በጋዜጣና መፅሄትም እኩል 60 በመቶ ነው። በሌላም በኩል አብዛኛዎቹ የመንግስት ተቋማት የማስታወቂያ በጀት የሚከፋፈለው ለሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ነው። በመንግስት የአገልግሎት ግዥ ሕግና መመሪያም የማስታወቂያና የስፖንሰርሽፕ አገልግሎትን በቀጥታ ለመንግስት መገናኛ ብዙሃን መስጠት የሚፈቀድ ሲሆን፤ የመንግስት ወጪን ከመቆጠብ ጋር በተያያዘም ለንግድ መገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያና ስፖንሰር መስጠት ይከለከላል። በተጨማሪም የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን በመንግስት የሚደጎሙ ሲሆን፤ የንግድ የመገናኛ ብዙሃን ግን አይደጎሙም። ይህም በሕዝብና በንግድ መገናኛ ብዙሃን መካከል ፍትሀዊ ውድድር አለመዘርጋቱን ያሳያል። ይህ መሆኑም የግል መገናኛ ብዙሃንን ከገበያ ሊያስወጣ ይችላል። ይህም በሕገ መንግስቱ ፕሬስ ጥበቃ ይደረግለታል የሚለውን ድንጋጌ የሚቃረን ይሆናል። በመሆኑም በሁሉም የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች ፍትሀዊ የሆነ የውድድር ስርአት እንዲጠናከር ይደረጋል።

ከዚህ አኳያም በሕዝብና በንግድ መገናኛ ብዙሃን መካከል ፍትሃዊ ውድድር መዘርጋት ይኖርበታል። ለዚህ እንዲረዳም ለሕዝብ የመገናኛ ብዙሃን ይፈቀድ የነበረው በአንድ ሰአት ውስጥ 12 ደቂቃ የማስታወቂያ ጊዜ ዝቅ እንዲደረግ እና በጋዜጣና መፅሄትም ለንግድ

ወይም ለግል ጋዜጣና መፅሄቶች በአንድ እትም ውስጥ ይፈቀድ የነበረው 60 በመቶ የማስታወቂያ ምጣኔ ወደ 80 በመቶ ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡

## 2.14 ማህበራዊ ሚዲያ

ማህበራዊ ሚዲያ የራሱ ጠቀሜታዎች ያሉት የመሆኑን ያህል ህዝብን ለሚጎዳ አላማም ሊውል ይችላል፡፡ የጥላቻ ንግግርንና አሳሳች መረጃን ለማሰራጨት፣ አመፅና ግጭት ለማነሳሳት፣ ለስም ማጥፋት ወይም ለሃሰተኛ ዜና ማሰራጫነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

ከመደበኛው መገናኛ ብዙሃን በተለየ ሁኔታ በማህበራዊ ሚዲያ የተሰራጩና የወንጀል ድርጊቶችን የያዙ ሁሉንም ይዘቶች፣ ይዘት አሰራጮችንና ተቀባዮችን ለይቶ ማጣራት ወይም መመርመርና በሕግ ተጠያቂ ማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ለዚህ የሚረዳ ማህበራዊ ሚዲያን የተመለከተ ራሱን የቻለ የሕግ ማዕቀፍ የለም፡፡

በመሆኑም በማህበራዊ ሚዲያ የሚለቀቁ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ይዘት ታማኝነትንና እውነተኛነትን ለማረጋገጥ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚውን ሕዝብ ስለአጠቃቀሙ ስነምግባርና ልዩ ልዩ  መመዘኛዎች ወይም ስታንዳርዶች በማስተማር የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄ መፍጠር ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ የማህበራዊ ሚዲያ አዎንታዊ ሚና ተጠቃሚነትን የሚያስተጓጉሉ ይዘቶች ሲኖሩ በተቻለ ፍጥነት እንዲወገዱ ለማድረግ የሚያስችል ስልት መከተል ይገባታል፡፡

በተጨማሪም በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት በሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች ላይ የሚታየውን የተዛባ የመረጃ ስርጭት ለመከላከል መንግስት እንደ መደበኛው መገናኛ ብዙሃን ሁሉ በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ የመገናኛ ብዙሃን ገፅ ባለቤቶች ወይም የመገናኛ ብዙሃን ይዘት አሰራጮች ማንነታቸውን በይፋ እንዲገልጹ የሚያስገድድ ሕግ ማውጣት ይጠበቅበታል፡፡ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት ተከታይ አገር በመሆኗ የአለም

አቀፍ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ ስራውን ቀድመው ከጀመሩት ዲሞክራቲክ አገሮች ተሞክሮ በመውሰድና ከአገራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመና አስቻይ የሆነ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም የፖሊሲ አቅጣጫ መከተል ይኖርባታል።

## 2.15 የህትመት መገናኛ ብዙሃን የወደፊት ዕድሎች

ለህትመት መገናኛ ብዙሃን ስርጭት ማነስ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ ጋዜጣና መፅሄቶችን ከአዲስ አበባ ውጭ በክልል ከተሞች ለማሰራጨት የሚያስችል በቂ የማሰራጫ አማራጭ መንገድ አለመኖር፣ የማተሚያ ቤት አለመስፋፋት፣ ለጋዜጣና መፅሄት ህትመት የሚጠየቀው የማተሚያ ዋጋ ከፍተኛ መሆን፣ የህብረተሰቡ የንባብ ባህል አለመዳበር፣ የመረጃ እጦት ወይም እጥረትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በመሆኑም መደበኛውን የህትመት መገናኛ ብዙሃን በህትመት ምርት፣ በማሰራጫ ዘዴ እና ቀጣይነቱን በማረጋገጥ ረገድ ለማዘመን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ሞዴሎችን መመርመር፣ ማጥናትና መተግበር ያስፈልጋል። ከዚህ ጎንም ዘመናዊና ያልተማከለ የማተሚያ ቤት ድርጅት እንዲቋቋምና ዘመናዊና አስተማማኝ የስርጭት ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን መሰራት ይኖርበታል። ይህ አቅጣጫ አዋጭነት የሚኖረው ሁሉም አሳታሚዎች አዲስ አበባን ጨምሮ በአገሪቱ በሚገኙ ክልሎች የሚዘጋጁ ህትመቶችን በዝቅተኛ ዋጋ ማሳተምና ማሰራጨት ሲችሉ ነው። የጋዜጣና መፅሄት የሥርጭት ሂደትንም በማዘመን በፖስታ ቤትና በሌሎች አማራጭ መንገዶች እንዲሰራጭ ለማድረግ የስርጭት ሂደቱን ዘመናዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.16 የመገናኛ ብዙሃን ድጋፍና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ

በኢትዮጵያ ለሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ከሚደረገው ድጋፍ ባሻገር ለንግድና ለማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን የሚደረግ ቀጥተኛ የሆነ የመንግስት ድጋፍ የለም። ስለሆነም መገናኛ

ብዙሃን የዜጎችን አስተሳሰብ በማነፅ ዜጎች በአገር ግንባታ እንዲሳተፉ የሚያደርግ በመሆኑ ከማንኛውም ዘርፍ በተሻለ ድጋፍና ማበረታቻ ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር መገናኛ ብዙሃኑን ለመደገፍ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

- በመገናኛ ብዙሃን መሳሪያዎች ላይ የተጣለውን ከፍተኛ የገቢ ቀረጥ መቀነስ፣ በተቻለ መጠን በአገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታም ማመቻቸት፣
- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ መስርያ ቦታ፣ ብድር፣ የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ ዕድል ማመቻቸት፣
- የዜና ወኪሎችን በማጠናከር መገናኛ ብዙሃን ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- የመንግስት ተቋማት የማስታወቂያና ስፖንሰርሽፕ በጀት በውድድር እንዲከፋፈል ማድረግ፣
- ከበይነ-መረብ ጋር የተሳሰረ ያልተማከለና ለሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ውጤቶች በሁሉም ቦታ ተደራሽ የሆነ ብሄራዊ የማተሚያ ቤት ማደራጀት፣
- የማተሚያ ቤት ወጪንና የመሸጫ ዋጋን መደጎም፣ የህትመት ግብአቶች፣ ወረቀትና ሌሎች ለህትመት ሥራ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ፣
- በቂ ማተሚያ ቤት መቋቋሙንና የግሉ ዘርፍ መሳተፉን ማረጋገጥ፣ አሳታሚዎችም በግልም ይሁን በጋራ የራሳቸው የማተሚያና የማሰራጫ አውታር እንዲኖራቸው መደገፍ፣
- ጋዜጣና መፅሄት በፖስታ ቤትና በመሰል አማራጭ ቴክኖሎጂዎች ታግዞ እንዲሰራጭ ማድረግ፣
- በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መሳሪያዎች፣ የህትመት ግብአቶችና አገልግሎቶች ላይ የተጣለውን ግብርና ታክስ በጥናት በመመስረት መቀነስ፣ የእፎይታ ጊዜ መስጠት፣
- መገናኛ ብዙሃንን ለማስፋፋት፣ ለመደገፍና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ በፋይናንስና በቴክኒክ የሚደገፉበትን አሰራር መዘርጋት፤ ለዚህም የድጋፍ ፈንድ በማቋቋም ወይም በተቆጣጣሪ አካሉ በኩል የድጋፍ ስራ ማከናወን ይገባል፡፡

## 2.17 የመገናኛ ብዙሃን ራስን በራስ ስለመምራት እና የጋዜጠኞች ማህበራት

መገናኛ ብዙሃን የራሳቸውን ጠንካራ ምክር ቤት በማቋቋም፣ የራሳቸውን የሙያ ሥነ ምግባርና መተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት፣ ለጋዜጠኞች ብቃት ማረጋገጫ በመስጠት፣ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንም በመመርመርና በመወሰን ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁንና በአሁን ጊዜ በአገራችን መገናኛ ብዙሃን ራሳቸውን በራሳቸው የሚመሩበትና የሚቆጣጠሩበት ደረጃ ላይ አልደረሱም፡፡

ስለሆነም የመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤቱን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት መገናኛ ብዙሃን ራሳቸውን በራሳቸው የሚመሩበትና የሚቆጣጠሩበትን ስልት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ምክር ቤቱም የራሱን የሙያና የስነ ምግባር ደንብና ኤዲቶሪያል የብቃት ደረጃ መመሪያ ወይም ስታንዳርድ በማውጣት የመገናኛ ብዙሃን ኤዲተሮችንና ጋዜጠኞችን አቅም መገንባት ይኖርበታል፡፡ ምክር ቤቱ ዜጎች፣ ድርጅቶችና የመንግስት ባለስልጣናት የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በሙያዊ ሥነ ምግባር ላይ ተመስርቶ በገለልተኝነትና በታማኝነት የመመርመር ግብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁሉንም ዓይነት የጋዜጠኛ ማህበራትን አጠቃሎ የሚያሰባስብ አንድ አገራዊ ማህበር መቋቋም አለበት፡፡ የሚቋቋመው አገር አቀፍ የጋዜጠኞች ማህበር ልዩ ልዩ ድጋፍ በማሰባሰብ የአገልግሎት አቅሙን በቀጣይነት እያጠናከረ የሚጓዝ መሆን አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ከተልዕኳቸው አኳያ በተናጠል የሚያደራጁዋቸው የሙያ ማህበራት መበረታታት አለባቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት አደረጃጀት ዋነኛ ግቡ ለኤዲቶሪያል ነጻነት ጥብቅና መቆም፣ የማህበሩን አባላት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ማስጠበቅ፣ የሙያ ብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድ አውጥቶ መተግበር፣ የጋራ ትብብርን ማሳደግ እና በመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የወጡ መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ለመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ማሳወቅ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይም ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት የሚደግፉ የሙያና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ሊበረታቱ ይገባል፡፡

## 2.18 የጋዜጠኞች ደህንነትና ጥበቃ

የኢትዮጵያ ሕጎች ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብትን ያረጋገጡ ቢሆንም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የመገናኛ ብዙሃንና የጋዜጠኞች ነፃነት ተገድቦ ቆይቷል። በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ፕሬስ በተቋምነቱ የሕግ ጥበቃ እንደሚደረግለትና የሙያ ነጻነቱም እንደሚከበር ይገልፃል። ስለሆነም የጋዜጠኞችን የስራ ነጻነት የሚያደናቅፉ፣ አደጋ ላይ የሚጥሉና ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረኑ የመገናኛ ብዙሃንና ሌሎች የሕግ ማዕቀፎች እንደገና መፈተሽና መሻሻል ይኖርባቸዋል።

በሙያ የዳበረ ጥልቀት ያለውና ሞጋች ዘገባ የሚያቀርብ ጋዜጠኛ መፍጠር ያስፈልጋል። በመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና በጋዜጠኞች የአሰራር ነጻነት ላይ የሚከሰት ጣልቃ ገብነትንና ተፅዕኖን ለመከላከል ለመገናኛ ብዙሃን ተቋማትና ጋዜጠኞች መብትና ደህንነት ሕጋዊ ጥበቃ ወይም ከለላ ማድረግ ያስፈልጋል። በአንፃሩም ጋዜጠኞችና የመገናኛ ብዙሃን አካላት የአገርንና የህዝብን ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይጥሉ የተጠያቂነት አሰራርንም መዘርጋት ያስፈልጋል።

## 2.19 የጋዜጠኝነት የሙያ ስነምግባር እና የብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድ

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን በአመዛኙ የሙያ ስነ ምግባርን በማክበርና የፕሮግራም ደረጃ መመዘኛዎችን ወይም ስታንዳርድን ጠብቆ በመስራት በኩል ሰፊ ውስንነት የሚታይበት ነው። በመሆኑም መገናኛ ብዙሃን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እራስን በራስ መቆጣጠር የሚያስችል የጋዜጠኝነት የሙያ ስነ ምግባርና የፕሮግራም ይዘት ስታንዳርድ ማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሁሉም ይዘቶች የሚቀርቡበት የራሳቸው የሙያ ብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድ ሊኖራቸው ይገባል። የዘገባና የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀትና የማስፈፀም አቅምን በመገንባት በዚህ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችንና ክፍተቶችን መፍታት ያስፈልጋል።

## 2.20 የዜና አገልግሎት

መገናኛ ብዙሃንና የኮሙዩኒኬሽን ልማት ያለጠንካራና ታማኝ የዜና ምንጭ ተቋም የሚታሰብ አይደለም። በመገናኛ ብዙሃንና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ የአገሪቱን የዜና አገልግሎት አሰራር፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ፈጻሚ አቅም፣ ቴክኖሎጂና ግብአት ዘመኑ ከደረሰበት የዜና አገልግሎት እድገት ደረጃ ማድረስ ይገባል። አሁን ባለዉ ሁኔታ በአገራችን የሕዝብ የዜና አገልግሎት በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን መገናኛ ብዙሃኑም በውጭ የዜና ምንጮች ላይ ጥገኛ ሆነዋል።

አገሪቷ አሁን ከደረሰችበት የእድገት ደረጃና እያደገ ከመጣው የህዝብ የመረጃ ፍላጎትና አለም አቀፋዊው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፈጣንና ተለዋዋጭ እድገት አንፃር የተቃኘ ወቅታዊና ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚንቀሳቀስ የህዝብ ዜና አገልግሎት ተቋም መገንባት የመንግስት የፖሊሲ ትኩረት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በቀጣይነት አማራጭ የግል የዜና አገልግሎቶች የሚስፋፉበትንና የሚጠናከሩበትንም አቅጣጫ መቀየስ አስፈላጊ ይሆናል።

## 2.21 የአቅም ግንባታ ስራዎች

የአገራችን መገናኛ ብዙሃን ለማህበራዊ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለፖለቲካዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማበርከት በሚያስችል ሁኔታ ብዝሃነቱን፣ ጥራቱን እና ተደራሽነቱን ጠብቆ አልተስፋፋም። የመገናኛ ብዙሃን ዘርፉን ሁለንተናዊ አቅም በቀጣይነት ከመገንባት አንጻር በቴክኖሎጂና በሰው ሀይል አቅም ግንባታ በመንግስት የሚደገፉና የራሳቸው ጠንካራ አደረጃጀት ያላቸው የማሰልጠኛ ተቋሞችን በማቋቋም በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የረጅምና የአጭር ጊዜ የስራ ላይ ስልጠናዎች በመስጠት የጋዜጠኞችን ሙያና ክህሎት ማሳደግ ያስፈልጋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ከክልልና ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ትስስር በመፍጠር የጥናትና

ምርምር ውጤቶችን ማዳረስና አቅም መገንባት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካሉም በዚህ ረገድ ሃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

### 2.22 የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል

የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል አደረጃጀትን በተመለከተም ገለልተኛነቱ የተረጋገጠ ሆኖ ከልዩ ልዩ የማህበረሰብ አካላት የተውጣጣ ቦርድ እና ለሙያው ብቁ የሆነ አመራር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካሉ የሚጠበቅበትን አላማ ከግብ ለማድረስ እንዲችል የሰው ኃይል፣ የፋይናንስና የቴክኒክ አቅሙ ሊገነባ ይገባል፡፡ እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነቱ መሻሻል ይኖርበታል፡፡ ሕገ መንግስቱን የሚተላለፍ የመገናኛ ብዙሃን ሲኖርም በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የመገናኛ ብዙሃን የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

በክፍል ሁለት የተመለከተው አጠቃላይ የፖሊሲ አቅጣጫ በሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ላይ የሚተገበር የጋራ የፖሊሲ ማእቀፍ ሲሆን፤ በዚህ ክፍልም እያንዳንዳዱ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ካለው የግል የሥራና አሠራር ባህሪ አንፃር በተናጠል ሊተገበር የሚገባው የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ በየፈርጁ ተለይቶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1. የሕትመት መገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

ጋዜጣው ወይም መጽሄቱ በህትመት ወይም በበይነ-መረብ አማካኝነት መቅረቡ ልዩነት ሳይደረግ ይህ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂ በሁሉም አይነት ጋዜጣ እና መጽሄት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የፖሊሲው ዋና መስፈርትም ፈርጀ ብዙ የህትመት ውጤት መጎልበት እና የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት መረጋገጥ ወሳኝ ነው በሚል መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

#### 3.1.1. በመንግስት የሚተዳደሩ ጋዜጦችና መፅሄቶች

- በመንግስት ባለቤትነት ስር ያሉ አገር አቀፍ ጋዜጦችና መፅሄቶች ሁሉንም የአገሪቱ ክፍሎች መሸፈን እና ለሁሉም ሕዝቦች መሰራጨት አለባቸው፡፡
- የመንግስት ጋዜጦችና መጽሄቶች ወደ ነጻና ገለልተኛ የሕዝብ አገልግሎት ህትመት መገናኛ ብዙሃን መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- አገር አቀፍ የመንግስት ጋዜጣና መፅሄት ለአገር አቀፍ እትም የጽሁፍ ዝግጅት የሚውል ግብአት ለማግኘት እንዲረዳ በክልል ደረጃ ካሉ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ተቋማት ጋር በመተባበር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

#### 3.1.2. የንግድ ጋዜጦችና መፅሄቶች

- የግልና የንግድ ጋዜጦችና መፅሄቶች በተቀመጠው አገራዊ የምዝገባ ስርዓት መሰረት ተመዝግበው ወደ ሥራ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡና ግብር እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡
- የንግድ ጋዜጦችና መፅሄቶች ሁሉንም የአገሪቱን ክፍሎች እንዲሸፍኑ ከክልል እና ከአካባቢ መገናኛ ብዙሃን ጋር በመተባበር በህትመት እና በስርጭት ሂደት ግብአቶችን በመለዋወጥ በጋራ እንዲሰሩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

### 3.1.3 የማህበረሰብ ጋዜጦችና መፅሄቶች

ለትርፍ ያልተቋቋሙ አነስተኛ የአካባቢ ወይም የማህበረሰብ ጋዜጦችና መፅሄቶች መበረታታት አለባቸው።

## 3.2 የብሮድካስት መገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

የብሮድካስት አገልግት ሠጪዎች መላውን ሕዝብ የመረጃ ተደራሽ የማድረግ፣ የማስተማርና የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው። እንዲሁም ለአገሪቱ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከምድር ወደ አየር ወይም በሳተላይት ወይም በኬብል በሚሰራጭ ብሮድካስት እና በኢትዮጵያ ሉአላዊ ክልል ውስጥ ባሉ ሌሎች የማሰራጫ መንገዶች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው።

- የሕዝብ፣ የንግድ ወይም የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ሰጪዎች ለሕዝብ መረጃ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
- መንግስትም ለዘርፉ ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል።
- ብሮድካስተሮች የሕዝብ ንብረት የሆኑ የማሰራጫ አውታሮችን፣ የአንቴና ምሰሶ እና መሰል መሰረተ ልማቶችን በመጠቀም ይዘታቸውን ማሰራጨት እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግና የመገናኛ ብዙሃን መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት ይገባል።
- መንግስት የብሮድካስት አገልግሎቶችን ለመምራት የሚያስችሉ ሕጎችን በማውጣት፣ በሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መሰረት የኢዲቶሪያል ነጻነትና ዋስትናቸው ተጠብቆ እንዲሰሩ ያደርጋል።
- በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የሕዝብ ብሮድካስተር ጨምሮ የክልል ብሮድካስተሮች በአደረጃጀት እና በኤዲቶሪያል ነፃነታቸውን ጠብቀው ህዝባዊ አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል።

- የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል ከሌሎች የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር ለብሮድካስት ስርጭት የሚውል አጠቃላይ አገር አቀፍ የሬዲዮ ሞገድ ድልድልና አጠቃቀም እቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡
- ለአገልግሎት ዝግጁ የሆኑ የብሮድካስት የሬዲዮ ሞገዶች ምደባ ከአለም አቀፍ የቴሌኮምዩኒኬሽን ህብረት እና ከሌሎች ተገቢነት ካላቸው ክልላዊ እና አለም አቀፋዊ አካላቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚፈፀም ይሆናል፡፡
- ለሕዝብ፣ ለንግድና ለማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የሚዘጋጀው የሬዲዮ ሞገድ ምደባ እና የፈቃድ መስፈርት በግልፅና በዝርዝር የሚወስንና የኢዲቶሪያል ይዘትን በተመለከተም አጠቃላይ መመሪያን የያዘ መሆን አለበት፡፡
- ተቆጣጣሪ አካሉ ቀላል፣ ግልጽና ፍትሃዊ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርአት መዘርጋት አለበት፡፡
- የብሮድካስት ፈቃድ ለማግኘት በሚዘጋጀው መስፈርት ውስጥም የተወሰነ መቶኛ በአገር ውስጥ ለተዘጋጁ ይዘቶች ትኩረት የሚሰጥ አስገዳጅ መስፈርት መካተት ይኖርበታል፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ህጻናትን፤ ወጣቶችን፤ ሴቶችን እና አካባቢን የሚመለከቱ ፕሮግራሞችን በመስፈርቱ ማካተት ይገባል፡፡
- በተጨማሪም ራሱን የቻለ የተለየ የትምህርት እና የሙያ፣ የዜና፣ የልጆች፣ የመዝናኛ ወይም የሃይማኖት ፕሮግራም ለማሰራጨትም የብሮድካስት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

### 3.2.1 የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት

- የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት በአገር አቀፍ ወይም በክልል የሚቋቋም ሆኖ ነጻነቱና ገለልተኛነቱ የተጠበቀ፣ በመንግስትና በራሱ ገቢ የሚተዳደር ይሆናል፡፡ የቦርድ አመራሩ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተውጣጡና በፌዴራል ወይም

በክልል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሾሙ ነጻና ገለልተኛ አካላት የሚመራ ይሆናል፡፡

- የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለፕሮግራም ልውውጥ እና አገራዊ ፕሮግራም በቂ ሽፋን እንዲሰጥ፣ መረጃን በጥራትና በወቅቱ ተደራሽ እንዲያደርግ፣ አገራዊ አንድነትን እንዲያጠናክር፣ ወጪ ቆጣቢ አሰራርን እንዲከተል በሚያስችል መልኩ እንዲመራ ይደረጋል፡፡
- የሕዝብ መገናኛ ብዙሃን ለአካባቢ የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የይዘት፣ የባለሙያ፣ የመሳሪያና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ለማህበረሰቡ የመረጃ ተደራሽነት የበኩላቸውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡
- ከውጭ አገር መገናኛ ብዙሃን ጋር መሰል የፕሮግራም ልውውጥ ቢደረግ የባህል፣ ቱሪዝምና፣ ኢንቨስትመንት ዘርፍን የሚያበረታታ ይሆናል፡፡
- አገር አቀፍ የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ ከአጠቃላይ የአየር ሰአቱ ውስጥ ቢያንስ 80 በመቶውን አገር ውስጥ ለተዘጋጁ ይዘቶች ማዋል ይኖርበታል፡፡
- የክልል የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ ከአጠቃላይ የአየር ሰአቱ ውስጥ 70 በመቶውን ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፤ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል ይኖርበታል፡፡
- አገር አቀፍ እና የክልል የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎቶች ለአገራዊ አንድነትና ሰላም መስፈን የሚረዱ የተለያዩ ይዘቶችን በማቅረብ ህብረተሰቡን ማስተማር አለባቸው፡፡
- አገር አቀፍ የህዝብ ብሮድካስት አገልግሎት የመረጃ ተደራሽ ላልሆኑና በገጠራቷ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚኖሩ ማህበረሰቦች መረጃን ተደራሽ ለማድረግ የስርጭት ሽፋኑን ማስፋት አለበት፡፡
- አገር አቀፍም ሆነ የክልል የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎቶች የአገር ውስጥ የይዘት ምርት አቅምን እና የሃሳብ ብዝሀነትን ለማሳደግ ለተባባሪ ፕሮግራም አዘጋጆች በመገናኛ ብዙሃን ተሳታፊ እንዲሆኑ፤ የፕሮዳክሽን መሳሪያዎችን ተከራይተው ይዘት ለሚያዘጋጁ የግል ፕሮግራም አዘጋጆችም ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 3.2.2 የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት

- የንግድ ብሮድካስተሮች ነፃነታቸው የተጠበቀ የንግድ ድርጅቶች በመሆን አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡
- የንግድ ብሮድካስተሮች በተሰጣቸው ፈቃድ ውስጥ የተጠቀሱትን የሕዝብ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታዎች ማክበር አለባቸው፡፡
- የንግድ የሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ከአጠቃላይ የአየር ሰዓታቸው ውስጥ 60 በመቶውን ፈቃድ የወሰዱበት አካባቢን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፤ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡
- አገልግሎታቸውን በክፍያ የሚያቀርቡ ብሮድካስተሮች ከቻናሎቻቸው ውስጥ ቢያንስ ሁለት አገራዊ የሕዝብ መገናኛ ብዙሃንን ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡
- ትኩረታቸውን በገጠር አካባቢዎች ላደረጉ ወይም በክልልና በአካባቢ ደረጃ ለሚቋቋሙ፣ ወይም ግጭትን በማስወገድ በሰላም ዙሪያ ለሚሰሩ፣ ትምህርታዊና እና ማህበራዊ ልማትን የሚያጎለብቱ ፕሮግራሞችን የሚያሰራጩ የንግድ ብሮድካስተሮች ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸውና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

### 3.2.3 የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት

- የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች ዲሞክራሲን፣ የማህበረሰቡን ዕውቀት፣ ባህል፣ ልምድ፣ ማህበራዊ ልማት፣ የእርስ በእርስ መስተጋብር፣ ሰላም እና መግባባትን የሚያጠናክሩ መሳሪያዎች በመሆን በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ሊቋቋሙ ይገባል፡፡ በተለይ የመገናኛ ብዙሃን በሌለባቸው፣ በኢኮኖሚ በጣም ዝቅተኛ በሆኑ እና የተለያዩ ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን እንዲቋቋም ትልቅ ድጋፍ ይደረጋል፡፡
- የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች ለትርፍ ያልተቋቋሙና በማህበረሰቡ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይዘትን በተመለከተ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም

ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ቡድኖችን የሚያካትት፤ ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኛ ያልሆነ፣ ከማንኛውም የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሀይማኖታዊ ወይም ከአገራዊ፣ ክልላዊ፣ አካባቢያዊ እና ባህላዊ ተፅእና ተቋም ነጻ መሆን አለባቸው፡፡

- የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን በአካባቢው ያሉ ሁሉንም ቋንቋዎች ወይም ማህበራዊ ቡድኖች ፍላጎት እንዲያሟላ እና በተቻለ አቅም ማህበረሰቡ በአስተዳደር፣ በይዘት ዝግጅትና በፋይናንስ እንዲሳተፍ ጥረት ይደረጋል፡፡
- የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች የፕሮግራሙን 70 በመቶ አካባቢውን ለሚመለከቱ ወይም በሌላ በተመሳሳይ የማህበረሰብ ብሮድካስት ለተዘጋጁ እና ስለማህበረሰቡ ጉዳይ ለሚያተኩሩ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡ ቀሪው የሥርጭት ጊዜ ክልላዊ ወይም አገራዊ ዜና፣ ወቅታዊ ጉዳይ ወይም የተለየ አርዕስተ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ሊሆን ይችላል፡፡
- የማህበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያዎች ገቢያቸውን ከማስታወቂያና ከሌሎች ልዩ ልዩ ምንጮች በማሰባሰብ ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- የማህበረሰብ ብሮድካስት ሲቋቋም በመክፈቻው ምዕራፍ እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለጣቢያው ማጠናከሪያ የሚሆን ድጋፍ ከንግድ መገናኛ ብዙሃን ከተሰበሰበ የአገልግሎት ክፍያና በመንግስት ከሚመደብ አመታዊ የድጋፍ በጀት ተውጣጥቶ ሊደገፉ የሚገባ ሲሆን፣ የድጋፍ በጀቱም በመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካሉ በኩል ሊከፋፈል ይችላል፡፡
- የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የማህበረሰቡ የመረጃ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማረጋገጫ መሳሪያ በመሆናቸው ለቀጣይነታቸው እና ለውጤታማነታቸው ሁሉን አቀፍ የቦታና የመሳሪያ አቅርቦት፣ የገንዘብ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ አመራርና አደረጃጀታቸውም በማህበረሰቡ በራሱ የሚመራ ይሆናል፡፡

## 3.3 የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

በኢትዮጵያ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያ በመደበኛው የብሮድካስት እና የህትመት መገናኛ ብዙሃን ስርጭት ላይ በአንድ በኩል መልካም የሚባሉ አጋጣሚዎችን፤ በሌላ በኩልም ተግዳሮቶችን ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም መልካም አጋጣሚዎቹን ለማስፋትና ተግዳሮቶቹን ለመቀነስ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡-

- የኢትዮጵያ የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት ሰጪዎች ገቢ በሚያስገኝ ስራ ላይ ከተሰማሩ በንግድ ቢሮ እና በግብር ሰብሳቢ አካላት መመዝገብ ያለባቸው ሲሆን፤ ከመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካልም ፈቃድና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት አባል በመሆን የምክር ቤቱን አሰራርና መመሪያ ተከትለው ሊሰሩና ሊተዳደሩ ይችላሉ፡፡
- የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና ማህበራዊ ሚዲያው የጋዜጣና መፅሄት ይዘት በማሠራጨት ሥራ ላይ ከተሰማራ መደበኛው ጋዜጣና መፅሄት በሚመራበት የሙያ ስነ ምግባርና ሕግ የሚመራ ይሆናል፣
- የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን እና ማህበራዊ ሚዲያው የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራም በማሠራጨት ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነም መደበኛ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስተሮች በሚመሩበት ሕግ እና ደንብ የሚመራ ይሆናል፡፡
- የበይነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን፣ ማህበራዊ ሚዲያ እና ኦንላይን ሚዲያ አገልግሎቶች ተለይቶ በሚወጣ የሙያ ስነ ምግባር ደንብ፣ የብቃት ደረጃ መመዘኛ ወይም ስታንዳርድና ሕጎች እንዲመሩም ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት

ፖሊሲው በሚከተሉት መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ይፈፀማል፡፡ የእንዳንዱም የማስፈጸም ሀላፊነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

4.1. የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ አካል፡- የመገናኛ ብዙሃንን በማስፋፋት፣ የአቅም ግንባታ ስራ በማከናወን፣ በመከታተልና በመደገፍ፤

4.2. የመገናኛ ብዙሃን፡- የመገናኛ ብዙሃንን ሚናና ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት በመወጣት፣ ሕዝብን በማገልገል፤

4.3. የመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤትና የጋዜጠኞች የሙያ ማህበራት፡- የዘርፉን እድገት በማረጋገጥ፣ መገናኛ ብዙሃን የሚመሩበትን የስነ ምግባር ደንቦች በማዘጋጀትና በማስተዋወቅ፣ መገናኛ ብዙሃን በሃላፊነት መንሳቀሳቸውን በማረጋገጥ፣ ልዩ ልዩ የድጋፍ ስራዎችን በመስራት፤

4.4. የትምህርት ተቋማት፡- ጥራቱን የጠበቀ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ለዘርፉ ባለሙያዎች ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት፤

4.5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌዴራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ የህዝብ ምክር ቤቶች፡- መገናኛ ብዙሃን የዲሞክራሲ ተቋማት እንደመሆናቸው ለመገናኛ ብዙሃን ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ፣

4.6. መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፡- ለመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፤

ለፖሊሲው ተፈፃሚነት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል፡፡